# መቼ ተግባር ታዬ?!

በሕያው ቃል

የምን ትጥቅ መፍታት?! የምን ሆያ ሆዬ?!
መፈክር አስወራጂ፣ መቼ ተግባር ታዬ?!

የምን ደጅ ጥናት ነው፣ ዙሪያ መሽከርከር?!
"ሥልጣን የህዝብ ይሁን!" የሚለው መፈክር፣ ሳይውል በተግባር?!

ለዴሞክራሲ፣ ላገር አንድነት፣
በግፍ የወደቀው፣ ባጋዚ ጥይት፣
የዚያ ጀግና ወጣት! የዚያ ሰማእት፣
የዚያች ጀግና ወጣት! የዚያች ሰማእት!
ደማቸው ጠፍ ሳይል፣ ምንጊዜ ተረስተው?!
ይሳብ ወደኋላ ፣ የትግል ቃላቸው?!
"ሥልጣን የህዝብ ይሁን ! " የሚል ጥያቄያቸው ? !

ከትግራይ ተራሮች፣ እስከ ቦሌ ፎቆች፣
ድብቅ እስር ቤቶች፣ ግልጽ ወህኒ ቤቶች፣
በግፍ ተወርውሮ፣ የታገተው ዜጋ፣
ከተቆለፈበት ሰንሰለት ሳይወጣ፣
የምን አትርሱኝ ነው፣ መግባት በቆረጣ?!
በትግል ለመነገድ፣ ማዘጋጀት ሻንጣ?!

ልጇዋ በአጋዚ፣ ጥይት ተገድሎባት፣
ገመድ የታጠቀች፣ ያች ምስኪን እናት !
ግፈኛው ህግ ቀርቦ፣ ፍትህ ሞግቶላት !
በአደባባይ በግልጽ፣ ብይን ሳይሰጣት !
የምን እጅ መስጠት ነው፣ ሆያ ሆዬ ማብዛት ? !
ትግል ጭዳ አድርጎ፣
ሰማዕት ጭዳ አድርጎ፣ ለመጋበዝ እራት ? !
ቃል እምነትን ክዶ፣ ህዝብን ለማስበላት ? !

ያዘነውም አባት፣ ልጁን በግፍ አጥቶ፣
ገዳዩን ተፋርዶ፣ ፍትህን አግኝቶ፣
አርባ ሳያወጣ፣ ካዘን ቤቱ ወጥቶ፣
የምን መሰለፍ ነው፣ በውስኪ ተራጭቶ፣
ከገዳዩ ጋራ ዳግም ለመዳራት ብርጭቆን አጋጭቶ ? !

ይልቅ እንሙትለት፣ ለዋናው መፈክር፣
የፈታህም ታጠቅ፣ የላላብህ ወጥር !
የህዝብ እስከሚሆን የሥልጣኑ መንበር !
የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብት ሁልዬ እስኪከበር !
ዜጋ በሀገሩ በነፃነት መሥራት፣ ችሎ መዘዋወር !

አማራጭ አቅርቦ፣ በአማራጭ ቦድኖ፣ ነፃ እስኪከራከር ！ ነፃ እስኪወዳደር ！

ትግል አታቀዝቅዝ፣ ይቅር መደናገር ！
የፈታህም ታጠቅ፣ የላላብህ ወጥር ！
የህዝብ እስከሚሆን፣ የሥልጣኑ መንበር ！

እመቃው ቀጥሎ፣ ግድያና አፈና፣
ስንቱ ቤት ፈራርሶ፣ እየሆነ ወና፣
ትግል ድልን ወልዶ፣ ጉተናው ሳይጸና፣
የምን ሆያ ሆዬ፣ የምንድን ጭፈራ፣
በአምባገነን ገዥ፣ የሚፈሰው እንባ፣ ሳይቆም ሳያባራ?!
በአጋዚ ጥይት የሚገደለው ሰው ደሙ ሳያባራ?!

ያፈናው መዋቅር፣ ሳይጠፋ ፈራርሶ፣
ሀገር እያስነባ፣ ደም በግፍ አፍስሶ፣
የምን እጅ መንሳት ነው፣ አጉል ተቅለስልሶ？ ！
ግብን ለማስጨንገፍ፣ ትግልን አልወስውሶ？ ！

የሲአይኤን ቅምጥ፣ የሞሳድን ጌኛ፣
ያን የድል ሾተላይ፣ የድል አጥቢያ አርበኛ፣
ትግል አጨናጋፊ፣ የውጤት ቀበኛ
የምን ፊት አዋላጅ፣ አድርጎ ማምጣት ነው፣ አሁንም ዳግመኛ？ ！

ይቅር መደናገር፣ ይቅር መፋዘዝ፣
ይቅር መዘናጋት፣ ትግል ማቀዝቀዝ፣
ካልወለደ አይድንም፣ የትግል እርጉዝ፣
የፈታህም ታጠቅ፣ የላላብህ ወጥር!
ህዝብ እስከሚረከብ፣ የሥልጣኑን መንበር!